Youth for Peace and Security Africa
ወጣቶች ለአፍሪካ ሰላምና ደኅንነት

<u>አመሠራት</u>፡- ወጣቶች ለአፍሪካ ሰላምና ደኅንነት ኔትዎርክ የተመሰረተው እና የተመዘገበው እ.ኤ.አ በ2012 በሀገረ **<u>ጋና</u>** ነው፡፡

<u>ራዕይ</u>፡- ሰላም የሰፈነባትና ያደገች አፍሪካን ማየት

-እ.ኤ.አ በ2026 50% የአፍሪካ ወጣት ወደዚህ ኔትዎርክ ማስገባት

<u>ተልዕኮ</u>፡- ትልቅ እና በቀጣይነት የሚሰራ የዜጎች ኔትዎርክ በመገንባት፡-

-በሰላም ግንባታ የወጣቶችን ንቁ ተሳትፎ ማረጋገጥ

-ምሩቅና በየአከባቢው የሚገኙ ስራ አጥ ወጣቶች፤ የስራ ፈጠራዎችን ማበረታታት እና መደገፍ

-የሰብአዊ መብት ጥሰት እና ወንጀልን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና ለማስቆም ከአፍሪካ ወጣቶች ጋር መስራት

<u>ዓላማ</u>፡-

1. ግጭቶችን እና ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሁሉም ዜጋ ባለቤትነት፣ ባለመፍትሔነት እና ኃላፊነት ማረጋገጥ
2. በአሸባሪዎች እና በውጪ ኃይሎች ሃሳብ የሚመራውን የአፍሪካ ወጣት ማስቆም
3. ግጭቶች እና የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በስፋት በሚስተዋሉባቸው አከባቢዎች ያለውን ሕገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር እና ወጣቶችን የማስታጠቅ ተልዕኮ መግታት
4. በአፍሪካ የሚንቀሳቀሱ አሸባሪ ኃይሎችን እና ሕገ-ወጥ ወታደራዊ እንቅስቃሴዎችን ማስቆም
5. ወንጀሎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በዜጎችና በፍትህ አካላት መካከል ያለውን የመተማመን እና በተግባቦት የመስራት ባህል ማዳበር እና ማበረታታት
6. በአፍሪካ ወጣቶች ዘንድ የበጎ-ፈቃደኝነት፣ የብሔራዊነት እና የሀገር ወዳድነት ስሜት ማረጋገጥ
7. አለም-አቀፋዊ አዋጆችን እና የየሃገሩን ሕገ መንግስታዊ ስርዓቶችን በመከተል ፤ ስለሰብአዊ መብት፣ ስለነፃነት እና ስለኃላፊነት ያለውን ግንዛቤ ማጠናከርና ማስጨመጥ
8. በዜጎችና በፍትሕ አካላት መካከል የሚፈጠሩ ክፍተቶችን በማጥበብ፤ ግጭቶችን በሰላማዊ እና ጥንቃቄ በተሞላበት አካሄድ መፍታትን ማበረታታትና መደገፍ
9. የአፍሪካ ኅብረት እና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዓላማዎችን ለማሳካት የወጣቶችን ብሎም የዜጎችን ንቁ ተሳትፎ ማረጋገጥ
10. የስራ ፈጣሪነት ስሜትን በአፍሪካ ወጣቶች ዘንድ ማየት እና መደገፍ

<u>ዋና መፈክር</u>፡- “የአፍሪካን ሰላምና ደኅንነት ማረጋገጥ ለተሻለ ዕድገት”

<u>የኔትዎረኩ ዋና ዋና ተግባራት</u>

1. በየአከባቢው በሚከሰቱ ጉዳዮች በቂ መረጃ መሰብሰብና ማደራጀት
2. በየአከባቢው የሚከሰቱ የእርስ በርስ ግጭቶችን መከላከል
3. በየአከባቢው ሰላምን ማረጋገጥ
4. ግጭቶችንና ወንጀሎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ከፍትሕ አካላት ጋር መስራት
5. በግጭቶች ሳቢያ የተጎዱ አከባቢዎችን መንከባከብና መደገፍ
6. በጤና፣ በአከባቢ ጥበቃ እና በሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ጥናቶችን መስራት እና የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ